# የከፍተኛ ትምህርት የስኮላርሺፕ ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 916/2014

## መቅድም

በሀገራችን ለትምህርት ጥራት ልዩ ትኩረት የተሰጠ መሆኑና የመምህራን ትምህርት ደረጃና ብቃት ቁልፍ በመሆኑ ለዘላቂና ሁለንተናዊ ልማት መረጋገጥ አስተዋጽዖ ማድረግ ይቻል ዘንድ የከፍተኛ ትምህርት የትምህርት እድል አሰጣጥን በስርዓት በመምራት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን፣ ተመራማሪዎችና ሰልጣኞችን አቅም መገንባት መንግስት በጽኑ የሚያምን በመሆኑ፤

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርት እድል አሰጣጥን ውጤታማ ለማድረግ ወጥ፤ ግልፅ፤ ፍትሃዊ ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ሌሎች ተቋማት ብቁና በቂ የሰዉ ሀይልን ለማፍራት አማራጭ ስኮላርሽፕ ፕሮግራሞችን በማበረታታት የመንግስትን በጀት እና ወጪ መቀነስ በማስፈለጉ፤

በመንግስት ዩኒቨርስቲዎች እና ሌሎች ተቋማት የተናበበ ስርዓት በመዘርጋት፣ በመምራትና በማስተዳደር ዉጤታማ የሆነ የከፍተኛ ትምህርት የትምህርት እድል አሰጣጥን ለመተግበር በሁሉም ደረጃ ተዓማኒነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት ስርዓት እንዲኖር በማስፈለጉ፣

የትምህርት ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 86 (5) በተሰጠው ስልጣንና ሀላፊነት መሰረት ተቋማት የተሟላ ነፃነት እስኪጎናፀፉ ድረስ ይህንን ለመንግስትና ለግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚ ሰራተኞች፣ ለሌሎች ተቋማት ሰራተኞች እና ለበትረ ሳይንስ ተማሪዎች የሚሰጥ የስኮላርሺፕ ማስፈጸሚያ መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 1 አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ **"የከፍተኛ ትምህርት የስኮላርሺፕ ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 916/2014"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አንቀፅ 2 አውጪዉ ባለሥልጣን**

የትምህርት ሚኒስቴር የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 86 (5) በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት ይህንን የከፍተኛ ትምህርት የስኮላርሺፕ ማስፈጸሚያ መመሪያ አውጥቷል፡፡

**አንቀፅ 3 ትርጓሜ**

1/ **"ሌሎች ሴክተር መስሪያ ቤቶች ማለት"** በጀቱ በፌዴራል ወይም በክልል መንግስት የሚመደብለት ሆኖ ተጠሪነቱ በየደረጃው ላሉ የመንግስት መዋቅር ውስጥ አስፈጻሚ፣ ህግ ተርጓሚ፣ ወይም ህግ አስከባሪ የመንግስት ተቋም ማለት ነው፣

2/ **"በትረ ሳይንስ ፕሮግራም ማለት"** በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ እና በኢንጂነሪንግ የሙያ መስኮች በልዩ ሁኔታ በውጭ ሀገራት ዩኒቨርሲቲዎች በመጀመሪያ፣ በሁለተኛና በሶስተኛ ድግሪ ፕሮግራሞችና በአጫጭር ስልጠናዎች ከውጭ ሀገራት የቴክኖሎጂ ውጤቶችን፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂን ትኩረት በማድረግ ተሞክሮዎችን ወደ አገር ቤት ለማስፋት ታስቦ የተዘጋጀ ልዩ የስኮላርሺፕ ፕሮግራም ነው፡፡

3/ **"የስልጠና ዕድል"** ማለት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ለአጭር ወይም ለረጅም ጊዜ የሚሰጥ የትምህርት እድል ነው፡፡

4/ **"የአጭር ጊዜ ስልጠና"** ማለት ሰልጣኙ ካለው ሙያ ጋር ተዛማጅ የሆነ ለተቋሙ ተልዕኮዎች መሳካት የሚያግዝ ከሶስት ወራት ያልበለጠ የአቅም ግንባታ ስልጠና ማለት ነው፡፡

5/ **"የረጅም ጊዜ ትምህርትና ስልጠና"** ማለት ሰልጣኙ ካለው ሙያ ጋር ተዛማጅ የሆነ እና የትምህርት ደረጃ ሊያሳድግ የሚያስችል እና ለተቋሙ ተልዕኮዎች መሳካት የሚያግዝ ስልጠና ማለት ነው፡፡

6/ **"ሰልጣኝ"** ማለት በመጀመሪያ ዲግሪ፤ በ2ኛ እና በ3ኛ ዲግሪ፣ በህክምና ትምህርት መስክ በስፔሻሊቲና ሰብ ስፔሻሊቲ እንዲሁም ሌሎች አጫጭር ስልጠናዎች ዕድል የተሰጠው ሰራተኛ ማለት ነው፡፡

7/ **"አገልግሎት"** ማለት ተወዳዳሪው ባለው የትምህርት ዝግጅት/ሙያ ተሰማርቶ የተገኘ የስራ ልምድ ነው፡፡

8/ **"የትምህርትና ስልጠና አበል"** ማለት ሰልጣኙ በትምህርትና ስልጠና ላይ ለሚቆይባቸው ጊዜያት እንዲከፈል የተፈቀደ የመኖሪያ፣ የምርምር፣ የጤና ኢንሹራንስ እና ለሌሎች ወጪዎች የሚውል የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡

9/ **"በመንግስት የተገኘ የትምህርትና ስልጠና ዕድል"** በመግንስት ለመንግስት ስምምነት እና መንግስት ከልማት አጋሮች ጋር በሚያደርገው ስምምነት የሚገኝ የአጭርና የረጅም ጊዜ የትምህርትና ስልጠና ዕድል ማለት ነው፡፡

10/**"በግል የተገኘ የትምህርትና ስልጠና እድል"** ማለት አንድ የአካዳሚክ ሰራተኛ በግሉ በመጻጻፍ ያገኘው የአጭር/ረዥም ጊዜ የትምህርትና ሥልጠና ዕድል ማለት ነው፡፡

11/**"ጆርናል"** ማለት በዩኒቨርሲቲዎች ወይም በምርምር ተቋማት ደረጃ የአካዳሚክና አካዳሚክ ነክ የሆኑ የጥናትና የምርምር ጽሁፎችን የሚያወጣ ደረጃዉ የተመሰከረለት ህትመት ነው፡፡

12/**"ፕሮሲዲንግ"** ማለት በዩኒቨርሲቲዎችና በምርምር ተቋማት ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ተቋማት ደረጃ በአውደ ጥናቶች ላይ የቀረቡ የጥናትና ምርምር ፅሁፎች የሚታተሙበት መድብል ነው፡፡

13/**"የሥራ ክፍል"** ማለት በመንግስት መስሪያ ቤቶች በተለያዩ የስራ መዋቅሮች ያለ የሲቪል ሰርቪስ አደረጃጀት አንድ ክፍል ማለት ነው፡፡

14/**"ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር"** ማለት በቅደም ተከተል የትምህርት ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ማለት ነው፡፡

15/የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላት በአዋጅ 1152/2011 ትርጉም ይይዛሉ፡፡

16/ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ አገላለጽ የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

**አንቀፅ 4 የመመሪያው አስፈላጊነት**

ሀገራችን ቅድሚያ ትኩረት ሰጥታ በለየቻቸው መስኮችና አሁን በመሰራት ላይ ያለውን የሀገራችንን የሰው ሀይል አቅም ግንባታ ትኩረት ባደረገ መልኩ ለማስኬድ የስኮላርሺፕ ማስፈፀሚያ በማዘጋጀት፤ የሚሰጡ የአጭርና የረጅም ጊዜ የስልጠና ዕድሎችን ጥራትና ብቃት ለማረጋገጥ፣ በምልመላና በትግበራ ሂደት ግልጽና ፍትሀዊ እንዲሆኑ ለማድረግ፤ አሰልጣኝ ተቋማት ለየትምህርት ፕሮግራሞቹ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ተማሪዎቻቸውን በውጤታማነት እንዲያስመርቁ እና ሰልጣኞች ለሚጠበቅባቸው ብቃት እንዲተጉ ለማስቻል ይህን የስኮላርሺፕ ማስፈጸሚያ መመሪያ ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

**አንቀጽ 5 የመመሪያው ዓላማ**

የዚህ መመሪያ ዓላማ በሀገራችን የስኮላርሺፕ ዕድሎችን ወጪ ቆጣቢ፣ ግልፅ፣ ፍትሀዊ፣ አሳታፊ እና በብቃት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

**አንቀጽ 6፡ የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በሁሉም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ በስኮላርሺፕ ፕሮግራም ተጠቃሚ የፌደራልና የክልል ሴክተር መስሪያ ቤቶች፣ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ተማሪዎች የስኮላርሽፕ ተጠቃሚዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 7፤ መርሆዎች**

ሀ. ግልፀኝነት

ለ. ፍትሃዊነት

ሐ. ጥራትና አግባብነት

መ. ብቃት

ሠ. ወጪ ቆጣቢ

# ክፍል ሁለት
# ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ለሌሎች ሴክተር መስሪያ ቤቶች የሀገር ውስጥ የስኮላርሺፕ አሰጣጥ

## አንቀጽ 8፡ ለመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሀገር ውስጥ ስኮላርሽፕ ለውድድር የሚያበቁ መመዘኛዎች

1/ ተወዳዳሪው የሙከራ ቅጥር ጊዜውን አጠናቆ ቋሚ የሆነና የሁለት ተከታታይ የስራ አፈፃፀም ውጤት ያለው (ላት) መሆን አለበት፡፡

2/ ስልጠናውን አጠናቆ የተመለሰ ሰልጣኝ ግዴታውን ሳይወጣ በሌላ ውድድር መሳተፍ አይችልም፡፡ ነገር ግን የስልጠናው አስፈላጊነት በተቋሙ አስተዳደር ካውንስል ወይም በአቻ አደረጃጀት ተገምግሞ ከታመነበት የተቀመጠውን ግዴታ ሳያጠናቅቅ ቀሪ ግዴታው ላይ ተጨማሪ ውል ገብቶ ሊማር ይችላል፡፡

3/ አንድ ሰልጣኝ የትምህርትና ስልጠና ዕድል ካገኘ በኋላ የሚሰራበትን ተቋም ፍቃድ ሳያገኝ ካቋረጠ ለአንድ ዓመት መወዳደር፣ ትምህርት ጀምሮ ማቋረጥ፤ የተሰጠውን እድል አለመጠቀም፣ ትምህርት ሳያጠናቅቁ ማቋረጥ አይቻልም፡፡

4/ ማንኛውም ሰልጣኝ ስልጠናውን በተመደበበት ተቋምና በተያዘለት ጊዜ መከታተል ይገባዋል፡፡ ሆኖም ግን በአሳማኝ ምክንያት ትምህርቱን ወይም ስልጠናውን መከታተል ያልቻለ ከሆነ ከሚመለከተው አካላት በሚቀርበው መረጃ መሰረት ታይቶ ቀጣይ ዓመት እንዲማር ይደረጋል፡፡

5/ በመንግስት ለሚገኝ የስልጠና ዕድል የመወዳደሪያ እድሜ ጣሪያ ለሁለተኛ ድግሪ 35 እና ለሶስተኛ ድግሪ ደግሞ 45 ዓመት ይሆናል፡፡

6/ በግል ሙሉ ወጪ ለሚገኝ የትምህርት ዕድል የዕድሜ ጣሪያ አይኖረውም፡፡

## አንቀጽ 9፡ የሀገር ውስጥ ስኮላርሺፕ ምልመላና መረጣ መስፈርቶች

1/ ለድህረ ምረቃ 2ኛና 3ኛ ዲግሪ፣ ስፔሻሊቲና ድህረ ስፔሻሊቲ ፕሮግራም ለሚወዳደሩ የአካዳሚክ ሰራተኞች የማወዳደሪያ መስፈርቶች ባላቸው የትምህርት ዝግጅት፣ ያስመዘገቡት የመመረቂያ ውጤት (CGPA)፣ የስራ ልምድ፣ የሁለት ጊዜ የስራ አፈጻጸም ውጤት፣ በከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በልዩ ልዩ

የኮሚቴ ነክ ስራዎች ላይ ንቁ ተሳትፎ፣ በጥናትና ምርምር/ ቴክኖሎጂ ሽግግር ተሳትፎ፣ በማኅበረሰብ አገልግሎት/ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ተሳትፎ፣ የሙያ መተዋወቂያ/ Induction training/ ስልጠና ተሳትፎ፣ የከፍተኛ ዲፕሎማ ስልጠና የወሰደ/ ከተቋሙ ባህርይ አንጻር ተመሳሳይ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ተሳትፎ እና የማህደር ጥራት ይሆናል (ዝርዝርና ዋጋው በአባሪ ተያይዟል)፡፡

2/ የሚሰጠው የትምህርትና ሥልጠና ዕድል የመምህራንን አቅምና ብቃት ማሳደግ ላይ ቅድሚያ ትኩረት ያደረገ መሆን አለበት፡

3/ ተወዳዳሪዎች የዩኒቨርስቲውን መግቢያ መስፈርቶችን (የመግቢያ ፈተና ማለፍ፣ ለውድድሩ የተቀመጠውን የትምህርት ደረጃ፣ የመመረቂያ ውጤት/CGPA እና በተቋማቱ የተቀመጡ ሌሎች ተጨማሪ የቅበላ መስፈርቶችን) ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፣

4/ ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች እና ልዩ የመማር ፍላጎት ላላቸው ተወዳዳሪዎች በህግ የተፈቀደው አዎንታዊ ማበረታቻ በምልመላው ሂደት ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፤

5/ የስራ ክፍሉ የተወዳዳሪዎችን ማመልከቻና ማስረጃ በአግባቡ በመያዝ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 የተመለከቱትን መመዘኛዎች ያሟሉትን ተወዳዳሪዎች ለስልጠና ምልመላና መረጣ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

6/ የስራ ክፍሉ ኃላፊ ተወዳዳሪ በሚሆንበት ጊዜ ለራሱ ጉዳይ ብቻ እንዲነሳ ተደርጐ በምትኩ ጊዜያዊ ሰብሳቢ በመስሪያ ቤቱ ኃላፊ እንዲወከል ይደረጋል፡፡ አንዱ ወይም ሁለቱም የኮሚቴ አባላት ተወዳዳሪ በሚሆኑበት ጊዜ በመስሪያቤቱ የበላይ ኃላፊ አማካኝነት ጊዜያዊ ኮሚቴ እንዲሰየም ይደረጋል፡፡

7/ የስራ ክፍሉ የስልጠና ምልመላና መረጣ ኮሚቴ የማወዳደሪያ መስፈርቶች አማካኝነት አመልካቾችን በማወዳደር አሸናፊውን በውጤት በመለየት በስራ ክፍሉ ኃላፊ ተፈርሞ ለሚመለከተው አካል ይላካል፡፡ ይህ በተዋረድ ላሉት የስራ ክፍሎችም የሚሰራ ይሆናል፡፡

8/ የስልጠና ዕድሉ የተሰጠው መስሪያ ቤት/ተቋም የበላይ ኃላፊ በማረጋገጥና በማፅደቅ ለሚመለከተው መስሪያ ቤት በመሸኛ ደብዳቤ ከአስፈላጊ መረጃዎች

ጋር እንዲላክ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም መረጃው በተዘጋጀ ቴክኖሎጂ ፕላት ፎርም እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

9/ በማንኛውም ደረጃ ምልመላና መረጣው ከተጠናቀቀ በኋላ የፀደቀው ውጤት ለሚመለከተው አካል በተለያየ ስልቶች ይፋ መሆን ይገባዋል፡፡

10/በተገኘው የስልጠና እድል የጥናቱ መስክ ያልተለየ ከሆነ የመሥሪያ ቤቱ የመስሪያ ቤቱ የማኔጅመንት ካውንስል በሚወስነው ውሳኔ መሰረት ሰራተኞች እንዲወዳደሩ ይደረጋል፡፡

11/የስልጠና እድል ሲመጣ ተወዳዳሪዎች በኢንተርኔት የሚያመለክቱበት ከሆነ የተቋሙን የስልጠና ፍላጎት ማዕከል በማድረግ የመሥሪያ ቤቱ የማኔጅመንት ካውንስል በሚወስነው ውሳኔ መሰረት አመልካቾች እንዲወዳደሩ ይደረጋል፤

12/የመሥሪያ ቤቱ የማኔጅመንት ካውንስል በሚወስነው ውሳኔ መሰረት በግልጽ ማስታወቂያ የሚመለከታቸው ሰራተኞች እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

13/ለትምህርትና ስልጠና እድል የሚወዳደሩ ሴት አመልካቾች ከወሊድ ጋር የሚገናኙ ጉዳዮች አስተማሪው ተቋም/ ሀገር በሚያወጣው ህግ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 10፡ በግል ስለሚገኙ የአጭርና የረጅም ጊዜ የትምህርትና ስልጠና እድሎች

1/ በአንቀፅ 9 የተጠቀሱት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ በግል የተገኘ የአጭርና የረጅም ጊዜ የትምህርትና ስልጠና እድል ለውድድር አይቀርብም፡፡

2/ አንድ ሰራተኛ በግሉ በመፃፃፍ በያዘው የትምህርት ደረጃ አቻ (የተለየ የደረጃ ለውጥ የማያመጣ) የትምህርትና ስልጠና ዕድል ለመማር ቢፈልግ ለተቋሙና ለሀገር የሚኖረውን የተለየ ፋይዳ በአሰሪ መስሪያቤቱ ሲታመንበት ብቻ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

3/ በግል የተገኘ የትምህርት ዕድል ከመንግሥት ምንም ዓይነት ድጋፍ የማይጠይቅ ከሆነ ከአሠሪ ተቋሙ ምንም የውል ስምምነት ሳይፈጽም መሄድ ይችላል፡፡

4/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ 3 የተጠቀሰ እንዳለ ሆኖ ከዚህ ቀደም የትምህርት እድል በተሰጠው የትምህርት እድል ያለበት/ባት ዕዳ ካለ ታሳቢ ተደርጎ ይከናወናል፤

5/ በግል የተገኘ የትምህርት ዕድል ከመንግሥት የድጋፍ ደብዳቤ ጀምሮ ድጋፍ የሚጠይቅ ከሆነ ከአሠሪ ተቋም ጋር ተመልሶ ለማገልገል የውል ስምምነት ይጠበቅበታል፡፡

## አንቀጽ 11፡- ለሌሎች ሴክተር መስሪያ ቤቶች የሚሰጥ የትምህርትና ስልጠና እድል የማወዳደሪያ ነጥቦች

1/ ተወዳዳሪዎች የዩኒቨርስቲውን የቅበላ መስፈርቶችን (የመግቢያ ፈተና ማለፍ፣ ለውድድሩ የተቀመጠውን የትምህርት ደረጃ፣ የመመረቂያ ውጤት /CGPA እና በተቋማቱ የተቀመጡ ተጨማሪ የቅበላ መስፈርቶችን) ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፣

2/ የሚሰጠው የትምህርት ዕድል በትምህርት ዘመኑ ያለውን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቅባለ አቅም እና የላኪ ተቋማት የበጀት ድጋፍ ታሳቢ በማድረግ የሚከናወን ይሆናል፣

3/ በዚህ መመሪያ ከተቀመጡ መስፈርቶች በተጨማሪ ለፌደራልና ለክልል ሴክተር መስሪያቤት ሰራተኞች የትምህርትና ስልጠና ዕድል የማወዳደሪያ መስፈርቶች ነጥብ አሰጣጥ በአገሪቱ የሰው ሀብት ልማት ድንጋጌዎችና በየመስሪያ ቤቶቹ የትምህርትና ስልጠና አሰጣጥ መመሪያ መሰረት የሚከናወን ይሆናል፤

4/ ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች እና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ አከባቢዎች እንደ ሀገር የተቀመጡ አዎንታዊ ማበረታቻዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

5/ የስልጠና ዕድል ፍትሃዊና ግልጽ በሆነ መንገድ በኮታ ለተቋማት የሚከፋፈል ይሆናል፡፡

6/ በመንግስት ለሚገኝ የስልጠና ዕድል የመወዳደሪያ እድሜ ጣሪያ ለሁለተኛ ድግሪ 35 እና ለሶስተኛ ድግሪ ደግሞ 45 ዓመት ይሆናል፡፡

7/ በግል ሙሉ ወጪ ለሚገኝ የትምህርትና ስልጠና ዕድል የዕድሜ ጣሪያ አይኖረውም፡፡

8/ ለትምህርትና ስልጠና እድል የሚወዳደሩ የሴት አመልካቾች ላኪው ተቋም/ሀገር ያለው አነስተኛ መስፈርት መሟላት እንደ ተጠበቀ ሆኖ ቅድሚያ እንዲያገኙ ይደጋል፤፤

### አንቀጽ 12፡ ለሌሎች ሴክተር መስሪያ ቤቶች የሚሰጥ ስኮላርሽፕ የምልምላና መረጣ መስፈርቶች

1/ የስልጠና እድሉ ሲመጣ ግልጽና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ በሚኒስቴር መስሪያቤቱ ድልድል ተሰርቶ የሚመለከታቸው ተቋማት እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

2/ የትምህርትና ስልጠና ጥናት መስኩ የሚያስቀምጣቸው መሰረታዊ መመልመያ መስፈርቶች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተግባራዊ ይደረጋሉ፤

3/ የሚመለከታቸው ተቋማት በተሰጣቸው ኮታ መሰረት የማወዳደሪያ መስፈርቶችን ተጠቅመው ያለፉትን ተወዳዳሪዎች የትምህርት ማስረጃዎችና ሌሎች ሰነዶች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለሚኒስቴሩ ያቀርባሉ፤

4/ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተወዳዳሪዎችን የትምህርት ማስረጃ በማጣራት የተቀመጡ መስፈርቶች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ የስልጠና እድሉን ለሰጠው አካል ይፋ ያደርጋል፤

5/ የተገኘው የትምህርትና ስልጠና እድል የጥናት መስክ ያልተለየ ከሆነ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት ተግባራዊ ይደረጋል፤

## ክፍል ሶስት

## የውጭ ሀገር የስኮላርሺፕ አሰጣጥ

### አንቀጽ 13፡ ለመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለውጭ ሀገር ስኮላርሽፕ ለውድድር የሚያበቁ መመዘኛዎች

1/ ተወዳዳሪው የሙከራ ቅጥር ጊዜውን አጠናቆ ቋሚ የሆነና የሁለት ተከታታይ የስራ አፈፃፀም ውጤት ያለው (ላት) መሆን አለበት፡፡

2/ ስልጠናውን አጠናቆ የተመለሰ ሰልጣኝ ግዴታውን ሳይወጣ በሌላ ውድድር መሳተፍ አይችልም፡፡ ነገር ግን የስልጠናው አስፈላጊነት በተቋሙ አስተዳደር ካውንስል ወይም በአቻ አደረጃጀት ተገምግሞ ከታመነበት የተቀመጠውን ግዴታ ሳያጠናቅቅ ቀሪ ግዴታው ላይ ተጨማሪ ውል ገብቶ ሊማር ይችላል፡፡

3/ አንድ ሰልጣኝ የትምህርትና ስልጠና ዕድል ካገኘ በኋላ የሚሰራበትን ተቋም ፍቃድ ሳያገኝ ካቋረጠ ቀጣይ ውድድር ሲመጣ ለአንድ ዓመት መወዳደር አይችልም፤

4/ የትምህርትና ስልጠና ዕድል ያገኘ ሰልጣኝ የተሰጠውን እድል አለመጠቀም፣ ትምህርት ሳያጠናቅቅ ማቋረጥ አይችልም፡፡

5/ ያለተቋሙ ፈቃድ ካቋረጠ ለትምህርትና ስልጠና የወጣውን ወጪ በገባው ግዴታ መሰረት በገንዘብ ወይም በአገልግሎት ይወጣል፡፡

6/ ማንኛውም ሰልጣኝ ስልጠናውን በተመደበበት ተቋምና በተያዘለት ጊዜ መከታተል ይገባዋል፡፡ ሆኖም ግን በአሳማኝ ምክንያት ትምህርቱን ወይም ስልጠናውን መከታተል ያልቻለ ከሆነ ከሚመለከተው አካላት በሚቀርበው መረጃ መሰረት ታይቶ ቀጣይ ዓመት እንዲማር ይደረጋል፡፡

7/ በመንግስት ለሚገኝ የስልጠና ዕድል የመወዳደሪያ እድሜ ጣሪያ ለሁለተኛ ድግሪ 35 እና ለሶስተኛ ድግሪ ደግሞ 45 ዓመት ይሆናል፡፡

8/ በግል ሙሉ ወጪ ለሚገኝ የውጭ ሀገር የትምህርት ዕድል የዕድሜ ጣሪያ የሚወሰነው በአሰልጣኙ ተቋም ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 14፡ ለመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሚሰጥ የውጭ ሀገር ስኮላርሺፕ ምልመላና መረጣ መስፈርቶች

1/ ለድህረ ምረቃ 2ኛና 3ኛ ዲግሪ፣ ስፔሻሊቲና ድህረ ስፔሻሊቲ ፕሮግራም ለሚወዳደሩ የአካዳሚክ ሰራተኞች የማወዳደሪያ መስፈርቶች ባላቸው የትምህርት ዝግጅት ያስመዘገቡት የመመረቂያ ውጤት (CGPA)፣ የስራ ልምድ፣ የሁለት ጊዜ የስራ አፈጻጸም ውጤት፣ በከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በልዩ ልዩ የኮሚቴ ነክ ስራዎች ላይ ንቁ ተሳትፎ፣ በጥናትና ምርምር/ ቴክኖሎጂ ሽግግር ተሳትፎ፣ የማኅበረሰብ አገልግሎት/ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ተሳትፎ፣ የሙያ መተዋወቂያ/ Induction training/ ስልጠና ተሳትፎ፣ የከፍተኛ ዲፕሎማ ስልጠና/ ከተቋሙ ባህርይ አንጻር ተመሳሳይ የአቅም ግንባታ ስልጠና የተሳትፎ እና የማህደር ጥራት ይሆናል (ዝርዝርና ዋጋው በአባሪ ተያይዟል)፡፡

2/ የሚሰጠው የትምህርትና ሥልጠና ዕድል የመምህራንን አቅምና ብቃት ማሳደግ ላይ ቅድሚያ ትኩረት ያደረገ መሆን አለበት፡

9/ የተወዳዳሪዎች የትምህርት ደረጃ እና የትምህርት ዝግጅት በየትምህርት ደረጃ የተቀመጠውን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቀጣይ የትምህርት ደረጃ የቅበላ መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆን ይኖርበታል፡

10/ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች እና ልዩ የመማር ፍላጎት ላላቸው ተወዳዳሪዎች በህግ የተፈቀደው አዎንታዊ ማበረታቻ በምልመላው ሂደት ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፤

11/የስራ ክፍሉ የተወዳዳሪዎችን ማመልከቻና ማስረጃ በአግባቡ በመያዝ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 የተመለከቱትን መመዘኛዎች ያሟሉትን ተወዳዳሪዎች ለስልጠና ምልመላና መረጣ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

12/የስራ ክፍሉ ኃላፊ ተወዳዳሪ በሚሆንበት ጊዜ ለራሱ ጉዳይ ብቻ እንዲነሳ ተደርጐ በምትኩ ጊዜያዊ ሰብሳቢ በመስሪያ ቤቱ ኃላፊ እንዲወከል ያደርጋል፡፡ አንዱ ወይም ሁለቱም የኮሚቴ አባላት ተወዳዳሪ በሚሆኑበት ጊዜ በመስሪያቤቱ የበላይ ኃላፊ አማካኝነት ጊዜያዊ ኮሚቴ እንዲሰየም ያደርጋል፡፡

13/የስራ ክፍሉ የስልጠና ምልመላና መረጣ ኮሚቴ የማወዳደሪያ መስፈርቶች አማካኝነት አመልካቾችን አወዳድሮ አሸናፊውን በውጤት በመለየት በስራ ክፍሉ ኃላፊ ተፈርሞ ለሚመለከተው አካል ይላካል፡፡ ይህ በተዋረድ ላሉት የስራ ክፍሎችም የሚሰራ ይሆናል፡፡

14/የስልጠና ዕድሉ የተሰጠው መስሪያ ቤት/ ተቋም የበላይ ኃላፊ በማረጋገጥና በማፅደቅ ለሚመለከተው መስሪያ ቤት በመሸኛ ደብዳቤ ከአስፈላጊ መረጃዎች ጋር እንዲላክ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም መረጃው በተዘጋጀ ቴክኖሎጂ ፕላት ፎርም እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

15/በማንኛውም ደረጃ ምልመላና መረጣው ከተጠናቀቀ በኋላ የፀደቀው ውጤት ለሚመለከተው አካል በተለያዩ ስልቶች ይፋ መሆን ይገባዋል፡፡

16/በተገኘው የስልጠና እድል የጥናቱ መስክ ያልተለየ ከሆነ የመሥሪያ ቤቱ የመስሪያ ቤቱ የማኔጅመንት ካውንስል በሚወስነው ውሳኔ መሰረት ሰራተኞች እንዲወዳደሩ ይደረጋል፡፡

17/የስልጠና እድል ሲመጣ ተወዳዳሪዎች በኢንተርኔት የሚያመለክቱበት ከሆነ የተቋሙን የስልጠና ፍላጎት ማዕከል በማድረግ የመሥሪያ ቤቱ የማኔጅመንት ካውንስል በሚወስነው ውሳኔ መሰረት አመልካቾች እንዲወዳደሩ ይደረጋል፤

18/የመሥሪያ ቤቱ የማኔጅመንት ካውንስል በሚወስነው ውሳኔ መሰረት በግልጽ ማስታወቂያ የሚመለከታቸው ሰራተኞች እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

19/ለውጭ ሀገር የትምህርትና ስልጠና እድል የሚወዳደሩ የሴት አመልካቾች ከወሊድ ጋር በተገናኘ አስተማሪው ተቋም/ ሀገር በሚያወጣው ህግ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 15፡ በግል ስለሚገኙ የአጭርና የረጅም ጊዜ የትምህርትና ስልጠና እድሎች

1/ በአንቀፅ 12 የተጠቀሱት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ በግል የተገኘ የአጭርና የረጅም ጊዜ የትምህርትና ስልጠና እድል ለውድድር አይቀርብም፡፡

2/ አንድ ሰራተኛ በግሉ በመፃፃፍ በያዘው የትምህርት ደረጃ አቻ (የተለየ የደረጃ ለውጥ የማያመጣ) የትምህርትና ስልጠና ዕድል ለመማር ቢፈልግ ለተቋሙና ለሀገር የሚኖረውን የተለየ ፋይዳ በአሰሪ መስሪያቤቱ ሲታመንበት ብቻ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

3/ በግል የተገኘ የትምህርት ዕድል ከመንግሥት ምንም ዓይነት ድጋፍ የማይጠይቅ ከሆነ ከአሠሪ ተቋሙ ምንም የውል ስምምነት ሳፈጽም መሄድ ይችላል፡፡

4/ በግል የተገኘ የትምህርት ዕድል ከመንግሥት የድጋፍ ደብዳቤ ጀምሮ ድጋፍ የሚጠይቅ ከሆነ ከአሠሪ ተቋም ጋር ተመልሶ ለማገልገል የውል ስምምነት ፈጽሞ መሄድ ይጠበቅበታል፡፡

## አንቀፅ 16፤ ለበትረ ሳይንስ ፕሮግራም ስኮላርሺፕ ለውድድር የሚያበቁ መመዘኛዎች

1/ የ12ኛ ክፍል አጠናቀው በተመደበቡት ዩኒቨርስቲ አንደኛ ዓመት ላይ ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች፣

2/ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመጀመሪያ ዲግሪ፤ በ2ኛ ዲግሪና በ3ኛ ዲግሪ በሳይንስ፣ በምህንድስናና ቴክኖሎጂ በማስተማር ላይ ለሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት መምህራን ብቻ፣

3/ ለ2ኛ ዲግሪና በላይ የትምህርትና ስልጠና ተወዳዳሪዎች ዕድሉ የሚሰጣቸው አስፈላጊ መረጃዎችን ማለትም የትምህርት የወጪ መጋራት እና የትምህርትና ሥልጠና መስኩ የሚጠይቃቸውን መረጃዎችን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

4/ በውጭ አገራት ለሚሰጡ የትምህርት እድሎች በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ /በተቀባይ ተቋማት የሚሰጠውን ፈተና ማለፍ ይጠበቅባቸዋል፤

5/ ተማሪዎች ምልመላና መረጣውን ካለፉ ከላኳቸው ተቋማት ጋር አስፈላጊውን የውል ስምምነት በማድረግ ትምህርታቸውን አጠናቀዉ ሲመለሱ ቅጥር መፈፀም ይጠበቅባቸዋል፡፡

## አንቀጽ 17፡- ለበትረ ሳይንስ ፕሮግራም የሚሰጥ የትምህርትና ስልጠና እድል የማወዳደሪያ ነጥቦች

በዚህ ፕሮግራም ሊታቀፉ/የእድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚገባው አመልካቾች

1/ ከዩኒቨርሲቲዎች በአንደኛ ዓመት ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ የተፈጥሮ ሳይንስ (ሳይንስ፣ ምህንድስናና ቴክኖሎጂ) ተማሪዎች፣

2/ መምህራን/ተመራማሪዎች በሳይንስ፤ በቴክኖሎጂ እና በኢንጂነሪንግ የሙያ መስኮች በልዩ ሁኔታ በሁለተኛና በሶስተኛ ድግሪ ፕሮግራሞችና በአጫጭር ስልጠናዎች ከውጭ ሀገራት ዩኒቨርሲቲዎች የቴክኖሎጂ ውጤቶችን፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂን ትኩረት በማድረግ ተሞክሮዎችን ወደ አገር ቤት ለማምጣት ተነሳሽነትና ጉጉት ያላቸው አመልካቾች፣

3/ የስልጠና ዕድል ፍትሃዊና ግልጽ በሆነ መንገድ የበትረ ሳይንስ ፕሮግራም ተልዕኮን በሚያሳካ መልኩ በኮታ ለተቋማት ይከፋፈላል፡፡

4/ በውድድሩ ተመርጠው ለትምህርት የሚላኩ ሠልጣኞች ከላኪው ተቋም ጋር ውል ስምምነት የሚፈርሙ መሆን ይጠበቅባቸዋል፣

5/ ስልጠናው በመንግሥት በተመረጡ ፕሮግራሞችና ዩኒቨርስቲዎች ብቻ የሚሰጥ ይሆናል፤

6/ በመንግስት ለሚገኝ የስልጠና ዕድል የመወዳደሪያ እድሜ ጣሪያ ለሁለተኛ ድግሪ 35 እና ለሶስተኛ ድግሪ ደግሞ 45 ዓመት ይሆናል፡፡

7/ ለትምህርትና ስልጠና እድል የሚወዳደሩ የሴት አመልካቾች ከወሊድ ጋር በተያያዘ አስተማሪው ተቋም/ ሀገር በሚያወጣው ህግ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 18፡ ለበትረ ሳይንስ ፕሮግራም የሚሰጥ ስኮላርሽፕ የምልምላና መረጣ መስፈርቶች

1/ ተወዳዳሪዎች የዩኒቨርስቲውን መግቢያ መስፈርቶችን (የመግቢያ ፈተና ማለፍ፣ ለውድድሩ የተቀመጠውን የትምህርት ደረጃ፣ የመመረቂያ ውጤት/CGPA እና በተቋማቱ የተቀመጡ ተጨማሪ የቅበላ መስፈርቶችን) ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፣

2/ የስልጠና እድሉ ሲመጣ ግልጽና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድልድል ተሰርቶ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

3/ ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች እና ልዩ የመማር ፍላጎት ላላቸው ተወዳዳሪዎች በህግ የተፈቀደው አዎንታዊ ማበረታቻ በምልመላው ሂደት ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፤

4/ የትምህርትና ስልጠና ጥናት መስኩ የሚያስቀምጣቸው መሰረታዊ መመልመያ መስፈርቶች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተግባራዊ ይደረጋሉ፤

5/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በተሰጣቸው ኮታ መሰረት የማወዳደሪያ መስፈርቶችን ተጠቅመው ያለፉትን ተወዳዳሪዎች የትምህርት ማስረጃዎችና ሌሎች ሰነዶች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለሚኒስቴሩ ያቀርባሉ፤

6/ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተወዳዳሪዎችን የትምህርት ማስረጃ በማጣራት የተቀመጡ መስፈርቶች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ ለሚመለከታቸው አካላት ይፋ ያደርጋል፤

7/ የተገኘው የትምህርትና ስልጠና እድል የጥናት መስክ ያልተለየ ከሆነ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት ተግባራዊ ይደረጋል፤

# ክፍል አራት
# ተግባርና ኃላፊነት

## አንቀጽ 19፡ የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

1/ **የትምህርት ሚኒስቴር**

ሀ. በተለያዩ ሀገራት ካሉ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንስላዎች ጋር በመቀናጀት የረጅምና የአጭር ጊዜ የትምህርትና ሥልጠና ዕድሎችን በማፈላለግ የመግባቢያ ስምምነቶችን ይፈራረማል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

ለ. የትምህርትና ስልጠና ዕድል መስፈርቶችን፣ ስታንዳርዶችን እና መመሪያዎችን ያዘጋጃል፣ ያሻሽላል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፡፡

ሐ. የትምህርትና ሥልጠና ዕድሎች ሲገኙ የስልጠና ምልመላና መረጣ ኮሚቴ በሰጠው ኮታ መሰረት ሰልጣኞችን እንዲልኩ ለአሰሪ ተቋማት የስልጠና ማስታወቂያዎችን ይልካል፡፡

መ. ከላኪ ተቋማት በውድድሩ የተላኩ ሰልጣኞች መረጃ የትምህርት ዕድሉን ለሰጡ ተቋማት/አካላት በስምምነቱ መሰረት በSoft/ በHard Copy/ በማደራጀት የተማሪዎችን መረጃ ይልካል፡፡ ለክትትል እንዲያመች ለኤምባሲዎች ያሳውቃል፡፡

ሠ. የትምህርትና ሥልጠና ዕድል ሲፈቀድ የሰልጣኞችን ዝርዝር መረጃ ወደ አሰሪ ተቋሞቻቸው ይልካል፡፡

ረ. ሰልጣኞች ከአሰሪ ተቋማት ጋር የውል ስምምነት መግባታቸው ሲረጋገጥ የመገጣጠሚያ ደብዳቤ በመስጠት የትምህርት ዕድሉን ወደ ሰጠው ተቋም ይልካል፡፡

ሰ. ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ የገንዘብ ክፍያዎችን በኤምባሲዎች በኩል እንዲፈጸም ይልካል አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡

ሸ. ለተማሪዎች የሚሰጡ ጥቅማጥቅሞችን በየጊዜው ካለው የኑሮ ሁኔታ አንፃር በማጥናት ለሚመለከታቸው አካላት እንዲከፍሉ ለውሳኔ ያቀርባል፤ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

ቀ. በውጭ ሀገራትና በሀገር ውስጥ የሚሰጡ ትምህርትና ስልጠናዎችን ውጤታማነት በማጥናት ማስተካከያዎችን ያደርጋል፣

በ. በውጭ ሀገራት ትምህርትና ሥልጠና አጠናቀው የሚመለሱ ሰልጣኞችን የመገጣጠሚያ ደብዳቤ ለላኪው ተቋም ይጽፋል፣ መረጃ ያደራጃል፣ ይከታተላል፡፡

ተ. እንደአስፈላጊነቱ ሚኒስቴሩ ከላኪና አሰልጣኝ ተቋማት ጋር በተማሪዎች የትምህርት ሁኔታ ዙሪያ በጋራ ወይም በተናጠል ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

ቸ. የበትረ-ሳይንስ ፕሮግራም ስኮላርሽፕ በማፈላለግ አሰልጣኝ ተቋማትን ከኤምባሲዎች ጋር ይመርጣል፣

ነ. ለትምህርትና ሥልጠና አመልካቾች ስኮላርሽፕ የሚሰጠው በጀት መኖሩ ሲያረጋግጥ ብቻ ይሆናል፡፡

**2/ የላኪ ተቋም**

ሀ. የመመሪያውን የስልጠና ዕድል መስፈርት ወይም ስታንዳርድ በግልጽ ለተወዳደሪዎች ያሳውቃል፣

ለ. የሥልጠና ውድድሩ ጥራትን ባማከለ አግባብ ግልጽ፣ ፍትሃዊና አሳታፊ በሆነ መንገድ ወቅቱን ጠብቆ ምልመላ መደረጉን በቃለ ጉባኤ በማስደገፍ የተመረጡ ሰልጣኞችን መረጃ አጠናቅሮ የትምህርት ዕድሉን ለሰጠው አካል በSoft/ በHard Copy/ በኦን ላይን ይልካል፣

ሐ. ለትምህርትና ሥልጠና የተላኩ ሰልጣኞች በተቀመጠው የቆይታ ጊዜ መሠረት ትምህርታቸውን ማጠናቀቅ መቻላቸውን ይከታተላል፣ ያላጠናቀቁትን አስመልክቶ ከአሰልጣኝ ተቋም ማብራሪያ በመጠየቅ ችግሩ እንዲፈታ ያደርጋል፣

መ. አንድ ሰልጣኝ አሳማኝ በሆነ ምክንያት ትምህርቱን በተቀመጠው የቆይታ ጊዜ ማጠናቀቅ ሳይችል ሲቀር ከአሰልጣኝ ተቋም ጋር ግንኙነት በመፍጠር ሰልጣኙ የመደበኛ ስራውን እየሰራ ትምህርቱን እንዲያጠናቀቅ ያመቻቻል፣

ሠ. በመመሪያው የተለዩ የሰልጣኞች መብትና ግዴታዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

ረ. የትምህርትና ሥልጠና ዕድል ያገኙትን የውል ስምምነት፣ ክሊራንስ፣ የወጪ መጋራት ስለማጠናቀቃቸው በማረጋገጥ ዝርዝር መረጃ ለሚኒስቴሩ ይልካል፡፡

ሰ. የስልጠናዉን ሂደት ለማስጨረስ ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ የደርሶ መልስ የትራንስፖርት፣ ቪዛ ለማስጨረስ እና የትምህርት ማስረጃ ለማረጋገጥ የሚወጡ ወጪዎችን ይሸፍናል፡፡

ሸ. አንድ ሰልጣኝ ውጭ ሀገር ለትምህርት በተላከበት የጊዜ ገደብ ውስጥ ማጠናቀቅ ባይችል ተቋሙ ባለው የአሠራር ሥርዓት መሠረት ትምህርቱን የሚያስቀጥለው ከሆነ አስፈላጊው ድጋፍ ተደርጎ እንዲያጠናቅቅ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ሰልጣኙ በተደጋጋሚ የትምህርት ጊዜ ቆይታ የማራዘም ዕድል ተሰጥቶት ከአሰልጣኝ ተቋማት በአካደሚክ ችግር ምክንያት ቢሰናበት እና ትምህርቱን በገዛ ፈቃዱ የሚያቋርጥ ከሆነ በውል ስምምነት መሠረት የከፍተኛ ትምህርት መምህር ሆኖ መቀጠል አይችልም፡፡ ለትምህርት የወጣውን ወጪ በውሉ መሰረት ለመንግስት ተመላሽ ያደርጋል፡፡

ቀ. በየሰሚስተሩ ተማሪዎች ያሉበትን ደረጃ (Academic Status) መረጃ በመያዝ ለተለያዩ ውሳኔዎች በግብዓትነት ይጠቀማል፣

3/ **የአሰልጣኝ ተቋማት**

ሀ. በትምህርት ሚኒስቴር በሚደረገዉ የተማሪዎች ምደባ መሰረት ባላቸዉ ሙሉ አቅም ተቀብለዉ ማሰልጠን፤

ለ. ዩኒቨርስቲው/ አሰልጣኝ ተቋሙ ለማስተማርና ለማሰልጠን የተቀበላቸውን ተማሪዎች የትምህርት ሁኔታ ይከታተላል፣ የየሰሚስተር ውጤታቸውን ለላኪ ተቋማት ያሳውቃል፡፡

ሐ. ለደረጃው ብቁ የሆነ የሰው ሀብትና ሌሎች ግብዓቶች በማሟላት የመማር ማስተማርና የምርምር ሂደቱ የጥራት ደረጃውን ጠብቆ እንዲከናወን ያደርጋል፡፡

መ. ለመማር ማስተማርና ለምርምር ድጋፍ የሚያወጣውን ወጪ መረጃ በመያዝ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፡፡

ሰ. ዝቅተኛ ውጤት ለሚያስመዘግቡ ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ በማድረግ ትምህርታቸውን በተቀመጠው የጊዜ ገደብ እንዲያጠናቅቁ ያደርጋል፡፡

ረ. በውጤት ማነስ ምክንያት የሚሰናበቱ ተማሪዎች/ ሰልጣኞችን ሁኔታ አስመልክቶ ከተጨባጭ መረጃዎች ጋር ለላካቸው ተቋም በወቅቱ ያሳውቃል፡፡

ሰ. በመንግስት በተወሰነው መሰረት ለመማር ማስተማርና ለምርምር የበጀት ድጋፍ ያደርጋል፡፡

ሸ. ሰልጣኞች በተቋሙ የአካደሚክ ካለንደር መሠረት በወቅቱ እንያጠናቅቁ ተግዳሮት የሆኑባቸውን ችግሮች በመለየት ለሚመለከታቸው አካላት ማብራሪያ ያቀርባል፡፡ መፍትሄም እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡

ቀ. አማካሪ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮችን በጊዜ የመመደብ ሀላፊነት ይኖርበታል፣

## 4/ የሰልጣኞች መብትና ግዴታ

### 4.1 . የሰልጣኞች መብት

ሀ. የትምህርትና ስልጠና ዕድል ማስፈጸሚያ መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት ደመወዝ እና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን የማግኘት፤

ለ. የውጭ ሀገር ሰልጣኞች በስልጠና ቆይታ ጊዜ በየወሩ የግማሽ ደመወዝ ክፍያ የሚያገኙ ሆኖ በሀገር ውስጥ የሚማሩ ከሆነ ግን ሙሉ የደመውዝ ክፍያ የማግኘት፤

ሐ. ማንኛውም ሰልጣኝ የአሰራር መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት በሥራ ላይ ለሚገኙ የአካዳሚክ ሰራተኞች በየጊዜው የሚሰጡ ጥቅማጥቅሞች የማግኘት፤

መ. በስልጠና ወቅት ቤተ ሙከራዎችን እና ወርክሾፖችን የመጠቀም እንዲሁም ሌሎች ለስልጠና የሚያስፈልጉ ድጋፎችን በነፃ ወይም በክፍያ የማግኘት፤

ሠ. ትምህርትና ስልጠናውን አጠናቆ ሲመለስ የተቋሙ አሰራር በሚፈቅደው መሰረት ደረጃው በሚመጥን ቦታ የመመደብ፣ ለቦታው የተፈቀደውን ጥቅማጥቅም የማግኘት፤

ረ. በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ትምህርትና ስልጠና ወቅት የሚፈጠር እርግዝና/ ወሊድን በተመለከተ ተማሪዎቹ በዊዝድርዋል ወደ ላኪው ተቋም

ተመልሰው ሙሉ ደመወዝ የማግኘት፤ የወሊድ ፈቃዳቸው ሲጠናቀቅ ትምህርታቸውን ካቆሙበት የመቀጠል፤

ሰ. የትምህርት አታሼ በሌላቸው ሀገራት ተማሪዎች በሚኒስቴር መስሪያቤቱና በኤምባሲዎቹ ድጋፍና ክትትል የማግኘት፤

ሸ. ሰልጣኙ በግሉ ያገኘው የውጭ አገር የአጭር ጊዜ ስኮላርሺፕ ከአንድ ወር በታች ሆኖ ትራንስፖርት ወጪ ስፖንሰርሺፕ የሰጠው አካል የማይሸፍን ከሆነ የደርሶ መልስ ትራንስፖርት እና የቪዛ ማስፈፀሚያ የማግኘት፤

ቀ. የትምህርት መረጃውን ዋናውን በተቋሙ አሰራር መሰረት ለሚመለከተው ክፍል ሲያስረክብ የመተማመኛ ሰነድ የማግኘት፤

በ. ሰልጣኙ የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሙ በመቋረጡ ወይም በሌላ አስገዳጅ ሁኔታ መቀጠል ካልቻለና ትምህርቱ ለሀገር ልማት ያለው ጠቀሜታ ተገምግሞ ሲፈቀድ የመጀመሪያውን ሴሚስተር ትምህርት ከማጠናቀቁ በፊት የመቀየር መብት ይኖረዋል፡፡

## 4.2 የሰልጣኙ ግዴታዎች

ሀ. በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ስልጠናውን ማጠናቀቅ፣ ያለበቂ ምክንያት ካቋረጠ ለቀጣይ አንድ ዓመት በሌሎች እድሎች የማይሳተፍ መሆኑ፣ በስልጠና ወቅት ያባከነው ወጪ ተሰልቶ የመክፈል ወይም ተጨማሪ ውል የመግባት፤ በውጭ ሀገራት ሰልጣኞችም በአሰልጣኝና በላኪ ተቋማት፣ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና በኤምባሲ ይከናወናል፣

ለ. ትምህርቱ የወሰደበትን ጊዜ እጥፍ ተመልሶ የማገልገል፤ ማገልገል የማይፈልግ ከሆነ ደመወዝን ጨምሮ የወጣውን ወጪ ከነቅጣቱ የመክፈል፣ መልቀቂያ ቢጠይቅ በውሉ መሰረት ያልሰራባቸው ጊዜያት ተሰልቶ ክፍያ ይፈጽማል፣

ሐ. በየሴሚስተሩ የደረሰበትን ደረጃ (Status) ለላከው ተቋም በጽሁፍ ያሳውቃል፣ ሰልጣኙ ስኮላርሺፑን ሳያጠናቅቅ ሌላ ትምህርት በዚያው ቢፈቀድለት ለቀጣዩ እድል ውል ሲይዝ ከዚያ በፊት ያልተወጣውን የውል ግዴታ ጨምሮ የመፈረም፤

መ. ለሚከፈለው የደመወዝ፣ ሌሎች የገንዘብና የማቴሪያል ድጋፎች ተመጣጣኝ ዋስ የማቅረብ፤

ሠ. ለትምህርትና ሥልጠና የተላከ ሰልጣኝ ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ የመመረቂያ ጽሑፍ አንድ ቅጂ ለሀገር አቀፍ በተመዛግብት/National Archieve/ እና አንድ ቅጂ ለላኪ ተቋም መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

ረ. በ3ኛ ዲግሪ መርሀ ግብር በሀገር ውስጥ ዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን የሚከታተል መምህር በአገልግሎት የማይያዝ 3 Cr.hr የማስተማር፤

ሰ. የእጩ ሰልጣኝ ውጤት በአሰልጣኝ ተቋም እስኪታወቅ ድረስ ለውጭ ሀገር ለ6 ወራት፣ ለሀገር ውስጥ ለ3 ወራት በሌላ የትምህርትና ስልጠና ውድድር መሳተፍ የማይችል መሆኑ፣

ሸ. የውጭ ሀገር ስልጠና የትምህርት መረጃውን ዋናውን በተገባው ውል እና በተቋሙ አሰራር መሰረት ለሚመለከተው ክፍል የማስረከብ፤

ቀ. ለ2ኛ ዲግሪ ከ2 ጊዜ በላይ ዕድል ተሰጥቶት መቀጠል ያልቻለ ሰልጣኝ በመማር ማስተማር ስራው መቀጠል የማይችል መሆኑ፣

በ. ትምህርት ከተጀመረ በኋላ የትምህርት መስክ መቀየር የማይቻል መሆኑ፣

ተ. በግል ለተገኘ የውጭ ሀገር ስልጠና የስልጠናው ጠቀሜታ በሚመለከተው አካል ከታመነበት ሰልጣኙ ተመልሶ ሊሰራ በተስማማበት የስራ ክፍል የሚያገለግል መሆኑ፣

ቸ. የወሊድ ፈቃድ በምትወጣበት ወቅት ሰልጣኟ የትምህርትና ስልጠና አበልና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን መጠየቅ የማትችል መሆኑ፣

# ክፍል አምስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 20፡ የተሻሩ መመሪያዎችና ሴርኩላሮች**

1. ከዚህ በፊት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የስኮላርሺፕ ትምህርትና ሥልጠና ማስፈፀሚያ ሆኖ ሲያገለግል የነበረው መመሪያ በዚህ መመሪያ ተተክቷል፡፡
2. ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ የአሰራር ልማድ በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 21፡ መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህ የስኮላርሺፕ ማስፈፀሚያ መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ በሚኒስቴሩ ሊሻሻል ይችላል፡፡

**አንቀጽ 22 መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ጸድቆ ከወጣበት ከግንቦት 25 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)

የትምህርት ሚኒስትር

## የሚከተሉት አባሪዎች የመመሪያው አካል ናቸው፡፡

## አባሪዎች

### አባሪ 1፡ የትምህርትና ስልጠና ወጪ አሸፋፈን

**ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ ሰልጣኞች የሚሰጥ ጥቅማ ጥቅምና አገልግሎቶች**

**በውጭ ሀገራት እና በሀገር ውስጥ በመንግስትና በአጋር አካላት ድጋፍ ለሚሰጠው ስኮላርሺፕ የሚሰጡ ጥቅማ-ጥቅሞችና ዋና ዋና አገልግሎቶች ከታች በሠንጠረዥ ቀርበዋል፡፡**

| የስኮላርሺፕ ዓይነት | የስልጠና ው ደረጃ | የወጪው ዓይነት | | | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | *ለስልጠና ክፍያ(Tution Fees)* | *ለትራንስፖርት ክፍያ* | *ለመኖሪያና ለመሳሰሉት* | *የምርምር ወጪ ለአንድ ጊዜ ብቻ* | *ለጽህፈት፣ ለጽህፈት መሳሪያ ግዥና የፎቶ ኮፒ አገልግሎት* | |
| 1/ በውጭ ሀገራት ለመንግስት ከፍተኛ ትምህርት አካዳሚክ ሠራተኞች የሚሰጥ ስኮላርሺፕ | 2ኛና 3ኛ ዲግሪ | በዓመት በአማካይ $5,000 | $800 * 4 /የምልልስ ብዛት) | በወር $350*12*4 በዓመት = 16,800 USD | በአሰልጣኙ ተቋም ወይም በላኪው መስሪያ ቤት ይሸፈናል | ለመኖሪያ እና ለመሳሰሉት ከተቀመጠ ወጪ | |
| 2/ በሀገር ውስጥ ለመንግስት ከፍተኛ ትምህርት አካዳሚክ ሠራተኞች የሚሰጥ ስኮላርሺፕ | 2ኛና 3ኛ ዲግሪ | በሚደረግ የግዴታ ውል ስምምነት ሚኒስቴሩ ትምህርት በነፃ ያስተምራል፣ | በወር ለአዲስ አበባ ብር 250፣ ከአዲስ አበባ ውጭ 150 | ለአዲስ አበባ ብር 1,000 ፣ ከአዲስ አበባ ውጭ 700 | ለ3ኛ ዲግሪ ተፈጥሮ ሳይንስ ብር 60,000፣ ማህበራዊ ሳይንስ ብር 45,000፣ 2ኛ ዲግሪ ተፈጥሮ ሳይንስ ብር 25,000፣ ማህበራዊ ሳይንስ 15,000 | በተመሳሳይ በየወሩ ብር 500 | |
| 3/ በሀገር ውስጥ ለግል ከፍተኛ ትምህርት አካዳሚክ ሠራተኞች የሚሰጥ ስኮላርሺፕ | 2ኛና 3ኛ ዲግሪ | በሚደረግ የግዴታ ውል ስምምነት ሚኒስቴሩ ትምህርት በነፃ ያስተምራል፣ | በሰልጣኙ/በላኪው ተቋም ይሸፈናል | በሰልጣኙ/በላኪው ተቋም ይሸፈናል | በላኪው ተቋም ይሸፈናል | በሰልጣኙ/በላኪው ተቋም | |
| 4/ በሀገር ውስጥ ለሌሎች ሴክተር መ/ቤቶች የሚሰጥ ስኮላርሺፕ | 2ኛና 3ኛ ዲግሪ | በሚኒስቴሩ ይሸፈናል | በሰልጣኙ/በላኪው ተቋም ይሸፈናል | በሰልጣኙ/በላኪው ተቋም ይሸፈናል | በሚኒስቴሩ ይሸፈናል | በሰልጣኙ/በላኪው መ/ቤት | |
| 5/ በውጭ ሀገራት ለበትረ ሳይንስ ፕሮግራም የሚሰጥ ስኮላርሺፕ | ከ1ኛ ዓመት ቅድመ ምረቃ ጀምሮ ሁሉም ተሳታፊዎች | በስምምነቱ መሠረት | በስምምነቱ መሠረት | በወር $350*12*4 በዓመት = 16,800 USD | በሚኒስቴሩ ይሸፈናል | ለመኖሪያ እና ለመሳሰሉት ከተቀመጠ ወጪ | |

**ማሳሰቢያ፡-**

**1/ በአባሪ 4 ሌሎች ዝርዝር የወጪ መረጃዎች እንደአስፈላጊነታቸው ቀርበዋል፡፡**

## አባሪ 2

1. ለመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ለሚወዳደሩ የአካዳሚክ ሰራተኞች የማወዳደሪያ መስፈርቶች ነጥብ አሰጣጥ

   ሀ. CGPA……………………………………………………………30%
   ለ. ለስራ ልምድ…...................................................................15%
   ሐ. የስራ አፈጻጸም ውጤት……………………..…………..……50%
   መ.የማህደርጥራት………………..…………………………..…...5%

2. ለ2ኛ ዲግሪ ትምህርት ለሚወዳደሩ የአካዳሚክ ሰራተኞች የማወዳደሪያ መስፈርቶች

### 2.1. ለዩኒቨርሲቲ መምህራን የነጥብ አሰጣጥ

ሀ.CGPA…………………………………………………………….30%
ለ. ስራ ልምድ …………….......................................................................5%
ሐ.የስራ አፈጻጸም ውጤት........................................................................45%
መ.በከፍተኛትምህርትናሥልጠናተቋማት...............................................5%
ሠ. የማኅበረሰብ …………………………..…………………..….5%
ረ.የሙያመተዋወቂያ/Induction/ ስልጠና/ ………………….…..5%
ሰ.የማህደርጥራት……………………………………………..…5%

### 2.2. ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አሰልጣኞች/ኢንስትራክተሮች የነጥብ አሰጣጥ

ሀ. CGPA ……………………………….…………..…………25%
ለ. ለስራ ልምድ/አገልግሎት.....................................................................5%
ሐ. የስራ አፈጻጸም ውጤት...........................................................................25%
መ.ኮሚቴ ተሳትፎ .................................................................................5%
ሠ. ለቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎች........................................................................ 20
ረ.ለኢንደስትሪኤክስቴንሽንስራዎች……………………….………15%
ሰ.የማህደርጥራት…………………………………………………....5%

## 3. ለ3ኛ ዲግሪ ትምህርት ለሚወዳደሩ የአካዳሚክ ሰራተኞች የማወዳደሪያ መስፈርቶች

ሀ.CGPA.......................................................................................................10%

ለ. አገልግሎት........................................................................................5%

ሐ. ስራ አፈጻጸም....................................................................................20%

መ. ኮሚቴ ነክ ጉዳዮች ………………………………………..…...10%

ሠ. ለጥናትና ምርምር/ቴክኖሎጂ ………………………………….25%

ረ. የማኅበረሰብ አገልግሎት …...……………………………… 15%

ሰ.የማህደርጥራት………………………………..……………….... 5%

ሽ.የከፍተኛዲፕሎማስልጠና/ ……………………………………….10%

**ማሳሰቢያ፡-** ከCGPA አመዛዘን ስርዓት ውጭ የሆነ የትምህርት ማስረጃ ላላቸው ተወዳዳሪዎች (ለምሳሌ ለቴ/ሙ/ት/ስልጠና አጠናቃቂዎች) በተቀሩት መስፈርቶች ተወዳድሮ ወደ 100% በመቀየር የሚሰላ ይሆናል፡፡

## አባሪ 3፡ የነጥብ አሰጣጥ፤

### ሀ/ የትምህርት ዝግጅት (CGPA) ውጤት ነጥብ አሰጣጥ፤

1) የCGPA ነጥብ ሲያዝ የተወዳዳሪው ውጤት በግሬድ የተገለጸ ከሆነ 4 ነጥብ ያለው ተወዳዳሪ በአባሪ አንድ ስር የተገለፀውን ነጥብ ያገኛል፡፡ ከ4 ነጥብ በታች ያለው CGPA ወደ መቶኛ እየተሰላ ውጤቱ ይሰጠዋል፡፡
2) የተወዳዳሪው ውጤት በቁጥር የተገለፀ ከሆነ ከዚህ ቀጥሎ በተገለፀው መሰረት ውጤቱ ወደ CGPA ተቀይሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
   a) [85-100]..........................A
   b) [80- 84) ........................A-
   c) [75-79)...........................B+
   d) [70-74)...........................B
   e) [65-69)...........................B-
   f) [60-64)...........................C+
   g) [50-59)...........................C
3) በአባሪ ሶስት ተራ ቁጥር አንድ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተወዳዳሪው በዉጭ ሀገር የተማረ ከሆነና ያስመዘገበው ውጤት በአገሪቱ የአካዳሚክ ፖሊሲ ከተደነገገው አነስተኛ እና ከፍተኛ የመመረቂያ ዉጤት የተለየ ቢሆንም በህጋዊ አካል የአቻ ግምት ከተሰጠው ተገቢውን ነጥብ እንዳመጣ ተቆጥሮ የማወዳደሪያ ውጤቱ ይሰላለታል፡፡
4) የተወዳዳሪው ውጤት ከ እስከ በሚል (Range) የተቀመጠ ከሆነ አማካይ ውጤቱ ተወስዶ በአባሪ ሁለት ተራ ቁጥር 1 እና 2 መሰረት ይሰላል፡፡
5) ለሶስተኛ ዲግሪ ተወዳዳሪዎች CGPA የሚያዘው የሁለተኛ ዲግሪያቸው ውጤት ብቻ ይሆናል፡፡ ስልጠናው የወሰደው ጊዜ በሰዓት የተቀመጠ ከሆነ በከፍተኛ ትምህርት አካዳሚክ ፖሊሲ ስርዓት ለአንድ “credit hour” የሚመደበው ስዓት ታስቦ የተቀመጠው ጊዜ ወደ “credit hour” ከተቀየረ በኋላ የተቀመጠውን የውጤት ድምር ለ“credit hour” በማካፈል “CGPA”ውን በማስላት ይተገበራል፡፡

### ለ/ የስራ ልምድ የነጥብ አያያዝ

1/ ተወዳዳሪው ከሚሰራበት ተቋም የተገኘ የአንድ አመት አገልግሎት አንድ ነጥብ ያገኛል፤

2/ የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና መምህራን/አሰልጣኞች ከሚሰሩበት ተቋም ውጭ ካሉ አቻ የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና/የምርምር ተቋማት የተገኘ አገልግሎትን በተመለከተ፡

ሀ. ከሌላ የግልም ሆነ የመንግስት ወይም አቻ ከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት/ ተገቢ ከሆነ ኢንደስትሪ ወደሚሰራበት ተቋም በህጋዊ ዝውውር ወይም መልቀቂያ መሰረት በቋሚ ቅጥር ለመጣ የአገልግሎት ነጥብ አያያዝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ለ. ከሌላ ተቋም በዝውውር ወይም በቅጥር የመጣ የአካዳሚክ ሰራተኛ አገልግሎቱ የሚያዘው በቅጥሩ ወይም በዝውውሩ ወቅት ያስያዘው ከሆነ ብቻ ይሆናል፡፡

3/ ተወዳዳሪው አንድ ዓመት የማይሞላ የአገልግሎት ዘመን ያለው ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም 2 የተደነገገውን መሠረት በማድረግ በወራት/በቀናት/ እየተመነዘረ ዋጋ ይሰጠዋል፡፡

4/ የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና መምህር/አሰልጣኝና ተመራማሪ ከሆነ ለውድድር የሚያዘው አገልግሎት አሁን የያዘውን የትምህርት እርከን ከያዘ ጀምሮ ያለው አገልግሎት ብቻ ነው፡፡

5/ አንድ ተወዳዳሪ በትምህርት የቆየባቸው ዓመታት እንደ አገልግሎት ተቆጥረው ለውድድር አይያዙም፡፡

6/ አምስት አመትና ከዚያ በላይ ያገለገሉ ተወዳዳሪዎች ሙሉ ነጥብ የሚያገኙ ይሆናል፡፡

## ሐ. የስራ አፈጻጸም ውጤት አያያዝ

1/ አንድ አመልካች ለትምህርትና ሥልጠና ውድድር ሲቀርብ ዉድድር ከሚደረግበት ሴሚስተር ጀምሮ ወደኋላ የሶስት ተከታታይ አማካይ የግምገማ ውጤት በአባሪ አንድ አንቀጽ 1-3 በተሰጠው ውጤት መሰረት ተሰልቶ ይያዝለታል፡፡

2/ አንድ አመልካች በተለያየ ምክንያት ዉድድር ከሚደረግበት ሴሚስተር ጀምሮ ወደኋላ የሶስት ተከታታይ አማካይ የግምገማ ውጤት ከሌለው እና ለትምህርትና ሥልጠና እንዲወዳደር በተቋሙ ከተፈቀደለት በቅርብ ያለው የስራ አፈጻጸም ውጤት ይያዝለታል፡፡

3/ ለትምህርትና ሥልጠና እድል ውድድር የሚቀርብ አመልካች የስራ አፈጻጸም ውጤት የሌለው ከሆነና እንዲወዳደር በልዩ ሁኔታ የተፈቀደለት  ከሆነ ለስራ አፈፃፀም ከሚያዘው ነጥብ ዜሮ ይሰጠዋል፡፡

4/ በስራ ባህርያቸው ምክንያት በየስድስት ወሩ የስራ አፈጻጸም ያልተሞላላቸው የተቋማት አመራሮች ለዚህ መስፈርት የተቀመጠውን ውጤት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

## መ. በከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በልዩ ልዩ ኃላፊነት፣ ኮሚቴና የኮሚቴ ነክ ስራዎች ነጥብ አሰጣጥ

1/ ለኃላፊነት ከተመደበው የነጥብ ድርሻ 60% የሚይዝ ሆኖ በኃላፊነት ተመድቦ ለሰራ የነጥብ አሰጣጡ በመሰረታዊ አመራርነት ለሰራ ለአንድ ዓመት አገልግሎት 1 ነጥብ፣ በመካከለኛ አመራርነት ለሰራ ለአንድ ዓመት አገልግሎት 1.5፣ በከፍተኛ አመራርነት ለሰራ ለአንድ ዓመት አገልግሎት 2 ነጥብ እየታሰበ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

2/ ለኮሚቴና ኮሚቴ ነክ ከተመደበው የነጥብ ድርሻ 40% የሚይዝ ሆኖ በአሰሪው ተቋም ውስጥ በተቋቋሙ የተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎች ተመድቦ ንቁ ተሳትፎ ማድረጉ በሚመለከተው አመራር ሲረጋገጥ በኮሚቴው ለአንድ የአገልግሎት ዘመን/Term/ ያገለገለ ለመስፈርቱ የተቀመጠውን ነጥብ ግማሽ፣ ሁለት ጊዜና በላይ ላገለገለ ለመስፈርቱ የተቀመጠውን ሙሉ ነጥብ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

## ሠ. ለጥናትና ምርምር/ቴክኖሎጂ ሽግግር /ተዛማጅ ስራዎች የነጥብ አሰጣጥ

በከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የደረጃ ዕድገት መመሪያ  ዝርዝር መስፈርቶች መሰረት የሚስተናገድ ሲሆን በደረጃ እድገት መመሪያው የማይካተቱ ተቋማት የራሳቸውን ዝርዝር መስፈርት አዘጋጅተው ይተገብራሉ፡፡

## ረ. የማህበረሰብ አገልግሎት / ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን/ ተዛማጅ ሥራዎች ነጥብ አሰጣጥ

በከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የደረጃ ዕድገት መመሪያ ዝርዝር መስፈርቶች መሰረት የሚስተናገድ ሲሆን በደረጃ እድገት መመሪያው የማይካተቱ ተቋማት የራሳቸውን ዝርዝር መስፈርት አዘጋጅተው ይተገብራሉ፡፡

**ሰ.የማህደር ጥራት ነጥብ አያያዝ**

**ለማህደር ጥራት የነጥብ አሰጣጥ በየተቋማቱ የውስጥ መመሪያ ዝርዝር መስፈርቶች መሰረት የሚከናወን ይሆናል፡፡**

**ሸ. የሌሎች ሀገራት የነጥብ አሰጣጥ ተሞክሮ እንደ ምሳሌ፤**

Converting foreign Countries Cumulative Grade Point Average (CGPA) into Ethiopian grading system of CGPA

$$Ethio_{CGPA} = 4 - \frac{Max_{CGPA} - Actual_{CGPA}}{Max_{CGPA} - Min_{CGPA}}$$

Where,

- $Ethio_{CGPA}$ is CGPA in Ethiopian grading system.
- $Max_{CGPA}$ is the maximum CGPA in foreign country grading system.
- $Min_{CGPA}$ is the minimum CGPA in foreign country grading system.
- $Actual_{CGPA}$ is the actual CGPA the student received in foreign country grading system.

**ወይም**

**ትምህርታቸውን በህንድ አገር ላጠናቀቁ ተማሪዎች**

**ምሳሌ፡-**

**ህንድ 10 ነጥብ ከፍተኛው ሲሆን ወደ ኢትዮጵያ 4 ነጥብ ለመለወጥ**

**አንድ ተማሪ በህንድ 8.44 ቢያመጣ 4.00*8.44/10 = 3.38 ይሆናል ማለት ነው፡፡**

ወይም

Example

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | Example | | | |
| | Ethiopia | Germany | Sweden (Lund University) | | |
| Max | 4 | 1 | 5 | | |
| | 3.75 | 1.8 | 4 | | |
| | 3.5 | 2.5 | 3 | | |
| | 3.25 | 3.3 | 2 | | |
| Min | 3 | 4 | 1 | | |

## አባሪ 4

### አባሪ 4/1 በተለያዩ አገራት በመንግስትና አጋር አካላት ድጋፍ ስኮላርሽፕ ዕድል ላገኙ ተማሪዎች በመንግስት የሚደረግ ድጋፍ

| ተ.ቁ | ስልጠና የሚሰጥበት አገር | ስልጠናው ስፖንሰር ያደረገው አካል | በመንግስት የሚሰጡ የስልጠና አበል አይነቶችና የክፍያው መጠን | | | | | | ለትምህርት የሚደረግ ክፍያ | የትራንስፖርት ክፍያ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የመኖሪያ አበል | የድጎማ | የምርምር | የመቋቋሚያ | የጤና ኢንሹራንስ በየዓመቱ | ቪዛና ሌሎች ወጪዎች | | | |
| 1 | ቻይና | በመንግስት ድጋፍ | $350 | - | $504 | $420 | በስምምነቱ መሰረት | በሚቀርብ ደረሰኝ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በመንግስት | |
| 2 | ቻይና | በቻይና መንግስት | በቻይና | $75 | የሚወሰን | - | በቻይና መንግስት | በሚቀርብ ደረሰኝ መሰረት | በቻይና መንግስት | በቻይና /በመንግስት | |
| 3 | ቻይና | በጋራ ድጋፍ | እስከ $150 | - | $504 | $420 | በቻይና መንግስት | በሚቀርብ ደረሰኝ መሰረት | በጋራ ድጋፍ | በመንግስት | |
| 4 | ህንድ | በመንግስት ድጋፍ | $350 | - | $504 | $420 | በስምምነቱ መሰረት | በሚቀርብ ደረሰኝ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በመንግስት | |
| 5 | ህንድ | በህንድ መንግስት | በህንድ | $218 | የሚወሰን | በህንድ | በቻይና መንግስት | በሚቀርብ ደረሰኝ መሰረት | በቻይና መንግስት | በህንድ በመንግስት | |
| 6 | ቱርክ | በቱርክ መንግስት | በቱርክ | 150/200 EURO | የሚወሰን | በቱርክ | በቱርክ | በሚቀርብ ደረሰኝ መሰረት | በቱርክ | በቱርክ | |
| 7 | ቱርክ | በመንግስት ድጋፍ | 560 EURO | 100/125 EURO | $504 | $420 | በስምምነቱ መሰረት | በሚቀርብ ደረሰኝ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በመንግስት | |
| 8 | ታይዋን | ታይዋን | ታይዋን | - | - | $2000 | በስምምነቱ መሰረት | በሚቀርብ ደረሰኝ መሰረት | በታይዋን | በመንግስት | |
| 9 | ሩሲያ | መንግስት | 410 | | | 250 | 250 | በሚቀርብ ደረሰኝ መሰረት | በሩሲያ | በመንግስት | |
| 10 | ኩባ | ኩባ | | 75 | - | - | ኩባ | በሚቀርብ ደረሰኝ መሰረት | ኩባ | በመንግስት | |
| 11 | ሰርቢያ | ሰርቢያ | | 100 | - | - | ሰርቢያ | በሚቀርብ ደረሰኝ መሰረት | ሰርቢያ | በመንግስት | |
| 12 | ኢራን | መንግስት | 300 | - | በተቋም | - | ኢራን | በሚቀርብ ደረሰኝ መሰረት | በኢራን | በመንግስት | |
| 13 | ጀርመን | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | |
| 14 | ፈረንሳይ | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | |
| 15 | ኮርያ | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | በስምምነቱ መሰረት | |
| 16 | ደ/አፍሪካ | መንግስት | - | የሀገር ውስጥ ድጋፍ | የሀገር ውስጥ ድጋፍ | - | በስምምነቱ መሰረት | - | በመንግስት | | |

ከላይ በዝርዝር ከተፈቀደው በመንግስት የበጀት ድጋፍ በውጭ ሀገር እና በሀገር ውስጥ ለሚሰጡ ስልጠናዎች ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ቀርቦ በቀን 21/05/04 ቁጥር መ190-1013/1 በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በተወሰነው መሰረት፡

1. ለስልጠና ክፍያ(Tution Fees) በዓመት በአማካይ $5,000 (አምስት ሺህ የአሜሪካን ዶላር) ለ3ኛ ዲግሪ እስከ 4 ዓመትና ለ2ኛ ዲግሪ 2 ዓመት በድምሩ $20,000 (ሀያ ሺህ የአሜሪካን ዶላር)

2. ለትራንስፖርት ክፍያ $800*4/የምልልስ ብዛት) = 3,200USD

3. ለመኖሪያና ለመሳሰሉት በወር $350*12*4 ዓመት = 16,800USD

   በድምሩ 40,000USD ሆኖ ለ2ኛ ዲግሪ ስልጠና የዚህ ወጪ ግማሽ ማለትም 20,000USD እንዲሆን በተፈቀደው መሰረት ድጋፍ ያደርጋል፣

## አባሪ 4/2፡ በሀገር ውስጥ ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ የሚሰጥ ጥቅማ ጥቅምና አገልግሎት

1/ ምንም አንኳ በተመራማሪ ተማሪዎች በድጋፉ ማነስ ቅሬታ እየቀረበ ቢሆንም በመንግስት የበጀት ድጋፍ በሀገር ውስጥ ለሚሰጡ ስልጠናዎች ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ቀርቦ በቀን 21/05/04 ቁጥር መ190-1013/1 በጽ/ቤቱ በተፈቀደው መሰረት መንግስት የሚከተሉትን ድጋፎች ያደርጋል፣

2/ በሚደረግ የግዴታ ውል ስምምነት ትምህርት በነፃ ያስተምራል፤

3/ የቤት ኪራይ ድጋፍ በየወሩ ለአዲስ አበባ 1,000 (አንድ ሺህ ብር) እና ከአዲስ አበባ ውጭ 700 (ሰባት መቶ ብር)፣

4/ የትራንፖርት ድጋፍ በየወሩ ለአዲስ አበባ 250 (ሁለት መቶ ሀምሳብር) እና ከአዲስ አበባ ውጭ 150 (አንድ መቶ ሀምሳ ብር)፣

5/ ለጽህፈት፣ ለጽህፈት መሳሪያ ግዥና የፎቶ ኮፒ አገልግሎት ድጋፍ በአዲስ አበባና ሌሎች ቦታዎች በተመሳሳይ በየወሩ 500 (አምስት መቶ ብር) ድጋፍ ያደርጋል፣

6/ የጥናትና ምርምር ድጋፍ፤

- ለ3ኛ ዲግሪ ተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፍ 60,000(ስድሳ ሺህ ብር)
- ለ3ኛ ዲግሪ ለማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ 45,000(አርባ አምስት ሺህ ብር)
- ለ2ኛ ዲግሪ ለተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፍ 25,000(ሀያ አምስት ሺህ ብር)
- ለ2ኛ ዲግሪ ማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ 15,000(አስራ አምስት ሺህ ብር) ለአንድ ጊዜ ብቻ ድጋፍ ያደርጋል፡፡